# ሕዝባዊ ዓመጽ ከፈነዳ የሚያግደው ኃይል አይኖርም

## ገላውዴዎስ አርኣያ

January 31, 2011

ሕዝብ ከተበደለና ከተጨቆነ የኋላ ኋላ መነሳቱ አይቀርም። የጊዜ ጉዳይ ነው። የህዝብ ዓመጽ ወይ ድንገተኛና ቅጽበታዊ ይሆናል ወይም ደግሞ ጊዜውን ጠብቆ በሂዳት የሚፈነዳ ሊሆን ይችላል። ብዙውን ጊዜ ስለ ሕዝባዊ ዓመጽ ወይም አብዮት ትንተና ሲደረግ የሚጠየቁ ሦስት ጥያቄዎች ቢኖሩ፡ 1) መንስኤአቸው ምንድነው ፣ 2) የዓመጹ ወይም አብየቱ ጸባዮች አስመልክቶ ከሌሎች ዓመጾች/አብዮቶች በምን ይለያል/ይመሳሰላል፣ 3) ሕዝባዊ ዓመጹ በሌሎች ሕብረተሰቦች ላይ እንድምታ ይኖሮዋል አይኖረውም የሚሉ ናቸው። ቆየት ብለን ስለ ዓመጾችና አብዮቶች ከታሪክ ጋር በማገናዘብና ምሳሌዎችን በመጥቀስ እናያቸዋለን፣ በመጀመርያ ግን የሁሉም ሕዝባዊ እንቅስቃሴ መፈክርና ዓላማ 'መሰረታዊ ለውጥ' የሚለውን መርህ እንደሚያስተጋቡና ብሎም የንቅናቄው ዓላማ ለመተግበር እንደሚጥሩ ማወቅ ይኖርብናል። ነገር ግን ማንኛውም ሕዝባዊ ዓመጽ በአርበኛ አብዮተኞች ወይም ለሃገር የሚቀረቀሩ ቅድመ-ግንባር ታጋዮች እስካልተመራ ድረስ ግቡን ይመታል ማለት አጠያያቂ ነው የሚሆነው።

የሕዝብ ዓመጽ 'መሰረታዊ ለውጥ' ጥያቄ በተለያዩ መንገዶች ሊንጸባረቁ ይችላሉ፦

1. የፍትሕ፡ የነጻነት፡ የእኩልነት፡ የሕዝቡ በፖለቲካ ያለው ተሳትፎ
2. ሕብረተሰቡን መልሶ መገንባት (reconstruction)
3. የተቋሞች ለውጥ፣ የመደብ መዋቅር ለውጥ፣ የድሮ ኋላ ቀር ልምዶችን ማስቀረት
4. አዲስ ራእይ
5. አብዮቱ ተልእኮ እንዳለውና ከአገር ድንበር አልፎም የሚቀጣጠል አድማሳዊ ባሕርይ እንዳለው ለማሳየት ወይም ለማሳመን መሞከር ወዘተ

ነገር ግን የማንኛውም አብዮት ጉዞና ባሕርይ መረዳት ብቻ ሳይሆን ስኬታማ ይሆናል ማለት የምንችለው የምሁራንና ሊሂቃን የርእዮተ ዓለም፡ ፕሮፓጋንዳ፡ የድርጅት እና አመራር ብቃት ሲኖርና የሕዝቡም የፖለቲካ ንቃተ ኅሊና ከአብዮቱ ሂደትና ግብ ተመጣጣኝ ሲሆን ብቻ ነው። አለዛ ቅጽበታዊ/ድንገተኛ የሕዝብ ዓመጾች ወይ ጊዜያዊ የሽግግር (liminary) መልክ/ጸባይ ይኖራቸውና ባክነው ይቀራሉ ወይም ደግሞ በአንጻሩ በሂደት በተደራጀ መንገድ ተጠናክረው ማእከላዊ ቦታ ይይዙና ከጊዜ ወደ ጊዜም ኃይል እየደለቡ ሲጓዙ ከቆዩ በኋላ አሮጌ፡ አድሃሪና ጨቋኝ ሥርዓቶችን ያወድቃሉ።

የሕዝባዊ ዓመጽ ወይም አብዮት መንስኤ ለማወቅ ግን በእውነቱ ጠለቅ ያለ ጥናታዊ ምርምር ይጠይቃል፣ ያም ሆኖም ለአብዮቱ ግፊት የሚያበረክቱ በርካታ ባህርያት የተወሳሰቡ ስለሆኑ በቅጡ መገንዘብ ያዳግታል። ነገር ግን በመጠኑም ቢሆን ሰፋ ባለ መልኩ የአብዮት መንስኤዎች በሦስት ይከፈላሉ፡

1. የመዋቅር ሁኔታዎች
2. ኅብረ-ስነልቦናዊ ቅድመ ሁኔታዎች
3. ልዩ የታሪክ ምክንያቶች

መዋቅርን አስመልክቶ ለምሳሌ በሕብረተሰቡ ዘንድ የመደብ ቅራኔ የጋለ ሁኔታ ላይ ሲደርስ ወይም ደግሞ በመንግሥትና በሕዝብ ዘንድ ቅራኔው ከተፋፋመ እንደ አንድ የሕዝብ ዓመጽ መንስኤ ሊሆን ይችላል።

ከዚሁ ከመዋቅር ሁኔታዎች የሚሄድ ደግሞ በምጣኔ ሃብታዊ ቀውሶች ምክንያት የፖለቲካ ሥርዓቱን የጨበጠ መንግሥት ሲዳከምና ከውስጡ ሲበሰብስ ሲሆን ፣ በተለይ ግን ምጣኔ ሃብቱ ያላግባብ ሲያዘቅጥና የዋጋ ግሽበት፣ የሥራ አጥነት (በተለይም በቅርቡ ከሥራ ተፈናቅለው ቦዘኔ የሆኑ ሰዎች ቍጥራቸው ሲበዛ)፣ ሰፊው ሕዝብ ደግሞ ባጠቃላይ ለድህነትና የዕለት ተዕለት የኑሮ ችግር ሲዳረግ ሕዝባዊ ዓመጽ ወይም አብዮት መፈንዳቱ አይቀርም።

የዋጋ ግሽበት ለረጂም ጊዜ ከቀጠለ ደግሞ ድሃው ብቻ ሳይሆን የሕብረተሰቡ ንዑስ ከበርቴና ከፍተኛው የመሃል መደቦቹን ስለሚነካም እነሱም ቢሆን የአብዮቱ ተዋንያን ይሆናሉ። አንዳንዴም በቅድመ ግንባር ይሰለፋሉ። የምጣኔ ሃብታዊ ውጣ ውረድ እና የዋጋ ግሽበት በቀለጠፈ ሁኔታ የሕዝቡ ሥነ ልቦናዊ ሁኔታ ይቀይሩታል፤ ሕዝቡ ለአመጽ ይዘጋጃል። በዚህ ጊዜ የሕዝቡ ንቃተ ኅሊና መዳበር ብቻ ሳይሆን ባንዳፍታ የሚፈጠሩ አብዮታውያን ብቅ ጥልቅ ይላሉ፤ ምልዓተ ሕዝቡ ደግሞ ምክንያት ብቻ ነው የሚፈልገው፤ ወደ አደባባይ በመፍሰስም የለውጥ መፈክሮችን ማስተጋባቱ አይቀርም።

ልዩ የታሪክ ምክንያቶች የተባሉትን እንደየ አገሩና እንደ ሁኔታው ይለያያሉ። በብዙ የምሁራን ጥናትና ምርምር ሰነዶች እንደተገለጸው 'ልዩ የታሪክ ወቅት' የሚባል አለ። ይህ የታሪክ ወቅት ታድያ በሰዎች (human agency) የሚተገበር ቢሆንም ቅሉ ከሰው ፍላጎትና ምኞት ግን ነጻ የሆነ ሂደት ነው። በሌላ አነጋገር የሰው ልጆች 'ልዩ የታሪክ ወቅትን' እንደፈለጉ በቍጥጥራቸው ማዋል አይችሉም ማለት ነው። ይኸንን በአብነት መግለጹ አስፈላጊ ይሆናል፦

የእንግሊዝ የ1688 አብዮት (አሸብራቂ አብዮት የሚሉት) ፣ የአመሪካ የ1776 የነጻነት አብዮት ፣ የፈረንሳዩ የ1789 የቡርዧ አብዮት ፣ የራሻ የ1917 የሾሻሊሰት አብዮት እና የቻይነው በ1949 የተገባበደደው (ሥር ነቀል ድርጊቱ ግን የቀጠለው) ሾሻሊስት አብዮት በሂደት ተጉዞው በልዩ የታሪክ ወቅት የፈነዱ ናቸው። ሁሉም የተደራጁ፣ በራእይና ርእዮተ ዓለም የተመሩ ሆነው ከእንግሊዙ አብዮት በስተቀረ ሌሎቹ ኃይልን በመጠቀምና ደም በማፍሰስ ነው ሥር ነቀል ለውጥ ያመጡት።

ሥር ነቀል ለውጥ ግን የሚመጣው በሕዝባዊ ዓመጽ ወይም አብዮት ብቻ አይደለም ፣ አብዮታዊ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች ግን ለውጥ ያመጡም እንደነ ህንድ፣ ታይላንድ፣ የከማል አታቱርክ ቱርክ እንደ አብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ኅብረ-ምጣኔ ሃብታዊ ለውጥ ያላመጡ ግን አሮጌው ሥርዓትን አስወግደው ነጻነት የተቀዳጁም

እንደ ላቲን አመሪካ አገሮች በምሳሌ መጥቀስ እንችላለን። የዚህ ዓይነት አብዮቶች በምልዓተ ሕዝቡ ቀስቃሽነት ሳይሆን ከላይ በሚጠነሰሱ 'የአናት አብዮቶች' ልንላቸው የምንችል አማካኝነት ነው የሚመሩት። በነኚ የአናት አብዮቶች እና በሥር ነቀል ሕዝባዊ አብዮቶች መሃል ልናስቀምጣቸው የምንችል እንደ የአልጀርያው ዓይነት አብዮቶች ደግሞ አሉ። የኢትዮጵያ የየካቲት '66 አብዮት ጊዜውን ጠብቆ የፈነዳ ሕዝባዊ ዓመጽ ስለነበር ከሥር ነቀል አብዮቶች ጋር ነው የሚመደበው። ሆኖም ግን የኢትዮጵያ የ'66 ሕዝባዊ ዓመጽ ወደ አብዮት ከመሸጋገሩ በፊት መሪሕ የተደራጁ፡ ራእይና ርእዮተ ዓለም ያላቸው ድርጅቶች ባለመኖራቸው በደርግ እንዲኮላሽ ተደርጓል። አብዮቱን መምራት የሚችሉ የተደራጁ ኃይሎች እንደ ኢህአፓ የመሰሉ ድርጅቶች ዓመጹ በሚቀጣጠልበት ሰዓት ገና ጨቅላዎች ስለነበሩ፣ የተደራጀ ኃይልም ወታደር ብቻ ስለነበር፡ ደርግ (ኢያ ጅቦ) በስመ-ሠራዊቱና በሕዝቡ ዓመጽ በመመጻደቅ አብዮቱን ቀለበሰው።

የጃፓኑ የ1868 የቱኩጉዋ ሥርዓትን ያወደቀና ያወደመ የመጇ አብዮት እንደ ትላልቆቹ የሥር ነቀል አብዮቶች አልነበረም ፣ ምክንያቱም የአብዮቱ መሪዎች የጃፓን ተሓድሶና የነበረውን የፖለቲካ ሥርዓትን መልሶ-መገንባት የሚል ዓላማና ግብ ነው የነበራቸው። ለዚህም ነው ከለውጥ በኃላ የንጉሳዊ አገዛዝ እንዲቀጥል ያደረጉት። የጃፓንን አብዮት የመሩት የሳሙራይ ታጣቂ ኃይሎች ስለነበሩ ፍላጎታቸው የነበረውን ሥርዓት ማሻሻል እንጂ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት አልነበረም ፣ በአዲስ ራእይና አዲስ ርእዮተ ዓለም የተካኑም አልነበሩም።

የሆኖ ሆኖ ግን የቶኩጉዋ ሥርዓት ራሱ በአዲስ የምጣኔ ሃብታዊ ኃይሎች (እንደ ነጋዴዎች የመሳሰሉት) ተወጥሮ ስለነበር አሮጌው የመሳፍንቱ ሥርዓት መንኮታኮት ጀምሮ ነበር። የዚሁ የአሮጌው ሥርዓት የምጣኔ ሃብታዊ ቋሚ መምርያም በመሰባበር ላይ ነበር። በተጨማሪም በቶኩጉዋ ጊዜ ዘመናዊ ትምህርት በጃፓን ተስፋፍቶ ስለነበረ የተማረው የኅብረተሰቡ ቍጥር ከመብዛቱም በላይ በዛው መጠንም የሕዝቡ ንቃተ ኅሊና ዳብሮ ስለነበር ለውጥን የሚደግፍ ሕዝብ እጅግ ብዙ ነበር። የመጇ ሳሙራይ ታድያ እንዲህ ያለ ሥርዓትን ነበር በቀላሉ የጣሉት።

ሁሉም አብዮቶች (ሥር ነቀሉና አናታዊ) ግን ምን ጊዜም ድል ይቀዳጃሉ ማለት አይደለም። ቀደም ብዬ የጠቀስኳቸውን አበይት አብዮቶች ፣ ከእንግሊዙ እስከ ቻይናው ስኬታማ ነበሩ። በአንጻሩ የጀርመን፡ የጣልያን፡ የስፓይንና የምስራቅ አውሮጳ የ1848 አብዮቶች ስኬታማ ያልሆኑ ወይም የወደቁ አብዮቶች ነበሩ። ለውድቀታቸው ዋና ምክንያት ደግሞ በነዚህ አገሮች፡ በተለይም በጣልያን፡ ስፓይንና ምስራቅ አውሮጳ የነበሩት መንግሥታት የመሾምና የውርስ መብት (patronage politics) ይጠቀሙ ስለነበሩና አብዮቱን ከበታች መምራት የሚችሉ ነጻ የሆኑ ሊሂቃን ባለመኖራቸው፡ ከነበሩም ደካማ በመኖራቸውም ጭምር ነው።

ከነዚሁ የወደቁ አብዮቶች ስብስብ የጀርመኑ ለየት የሚያደርገው ግን ስኬታማ ሊሆን ያልቻለው ፣ 1) የጀርመን አብዮተኞች በመከፋፈላቸውና አንድ ሃገራዊ ድርጅት ባለመፍጠራቸው ፣ 2) ጀርመን ራሱ አንደ ሃገር የተዋሃደ ብሔረ-መንግሥት አለመኖሩን ነው። በእንዲህ ዓይነት የፖለቲካ ክስተት ፣ በተለይም አብዮቱን ይመራሉ ተብለው የሚጠበቅባቸው ምሁራንና ሊሂቃን ዘንድ ፍኩክር ከተፈጠረና

ከተከፋፈሉ በቀውጢው ሰዓት ነጣቂ አሞራ ይመጣና የሁኔታውን አመቺ ሁኔታ በመጠቀም ሥልጣንን ይጨብጣል ፣ የዚሁ ክስተት ዓይነተኛ ምሳሌ የቻንስለር ቢዝማርክ ሥልጣን ላይ መውጣት ነው።

አብዮቱ ከወደቀ በኋላ ደግሞ የቀውጢው ፖለቲካ የፈጠረውን ነጣቂ አሞራ (ደርግ በኢትዮጵያ እንደ አብነት መጥቀስ ይቻላል) የተከፋፈሉትን አብዮተኞችን ቀስ በቀስ ይጠርግና ድጋፍ ያደረጉለትን ሊሂቃን ሳይቀር ይጨርሳል። ሕዝቡንም በኃይልና በጠበንጃ መግዛት ይጀምርና ተቀጣጥሎ የነበረውን አብዮት መጀመርያ ያኮላሻል፣ ቀጥሎም ከአብዮተኞቹ የሰረቀውን (የኮረጀውን) መርህ፡ መፈክር፡ ርእዮተ ዓለም ወዘተ እንደ መምርያ ይጠቀምና በአብዮቱ ስም ሰፊውን ሕዝብ ይጨቊናል። ከሕዝብ ጋርም ቅራኔ ውስጥ ይገባና አንዳንድ የሕብረተሰቡ አባላት የትጥቅ ትግል ይጀምራሉ። እነኚ ታጣቂ ኃይሎች በሁለት ልንከፍላቸው እንችላለን፡ 1) የተጨናገፈውን አብዮት እንደገና ለማንሰራራት የሚታገሉ ፣ 2) በአብዮት ስም በስልጣን ላይ ቊጢጥ ያለውን ብቻ በማስወገድ ራሳቸውን ሥልጣን ለመያዝ ጠበንጃ የሚመዙ ናቸው። የመጀመርያው ከተሳካለት ሥር ነቀል ለውጥ ነው የሚያመጣው ፣ የኋለኛው ከቀናው ደግሞ ጉልቻን ቢቀያይሩ ወጥ አይጣፍጥም ነው የሚሆነው። የሆኖ ሆነ ግን በቀውጢ ቀን ሥልጣን የያዘውን ቡድን ከሕዝቡ ጋር ቅራኔ ውስጥ ይገባና ቀስ በቀስ ደግሞ ከምልአተ ሕዝቡ ስለሚነጠል የታጠቁ ኃይሎችም ቀስ በቀስ ይጠናከሩና ክፉኛ ይመቱታል። አብዮቶኞቹ ከመቱትና ካወደቁት አሁንም ቢሆን መሰረታዊ ለውጥ ያመጣሉ ፣ ሥልጣን ፈላጊ ታጣቂ ኃይሎች ካቸነፉትና ሥልጣን ከያዙ ግን መጠነኛ ለውጥ እንጂ ጥልቀት ያለው ኅብረ-ምጣኔ ሃብታዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ሊያመጡ አይችሉም ወይም አይፈልጉም። እንደዚህ ያሉ ታጣቂ ኃይሎች ከፍ ብለን እንዳየነው ነጣቂ አሞራ ሳይሆኑ ሚናቸው እንደ ጥንብ አንሳ ነው የሚሆነው ፣ ምክንያቱም የመንግሥቱን ወታደር ቀስ በቀስ ነው የሚጠርጉት፣ እግረ መንገዳቸው ደግሞ የወደቀውን እያነሱ መንግሥቱ እጁ እስከሚሰጥ ወይም እስከሚፈረጥጥ ድረስ በለቀሙት ምርኮ ይሰነብቱና በትረሥልጣኑን ይጨብጣሉ። ቀደም ብሎ የተከሰተውን የአብዮት ፍንዳታ ደግሞ በጊዝያዊ መልክ ያከትማል።

አብዮቱ ውድቅ የሚሆነው ግን በነጣቂ አሞራና በጥንብ አንሳ በተጫወቱት ሚና ብቻ አይደለም። ቀደም ብለው በቅድመ ግንባር ተሰልፈው የነበሩት አብዮተኞች ስለተከፋፈሉ፡ የፈጠሩትን ድርጅት በአንጃነት ስለሰነጣጠቁት እና ፍኩክር ውስጥ ስለተነከሩ ለአብዮቱ ውድቀት አስተዋጽኦ ስላደረጉም ጭምር ነው። ከዚህም በላይ፡ ከነዚሁ አብዮተኞች በርካተው ከፍል የአብዮቱን ጉዳይ እርግፍ አድርጎ በመተው በዕለታዊ ኑሮው የሚሰማራ ሲኖር ፣ በተቃዋሚ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ ደግሞ ከዓብይና ሃገራዊ አጀንዳ ወደ ጎሳ ፖለቲካ በማዝቀጥ አብዮታዊ ሳይሆን ጸረ-አብዮታዊ ሚና ስለሚጫወቱ ምልአተ ሕዝቡን አቅፎና አስተባብሮ ይንቀሳቀስ የነበረውን ንቅናቄ ቢያከትምም የሚያስደንቅ አይሆንም።

የኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ወይም የኢትዮጵያን ተማሪዎች ንቅናቄ በቅድመ የካቲት በቅጡ የሚያውቁ ኢትዮጵያውያን ከመሬት ላራሹ ጎን ለጎን የብሔር ጥያቄ የንቅናቄ ዋነኛና አንገብጋቢ ጥያቄ ነበር። የብሔር ጥያቄ የዴሞክራሲ ጥያቄ ነው ፣ ብሔሮቹም የኢትዮጵያ ክፍላተ-አካላት ስለሆኑ የአንድ ሰውነት አካል ከታመመ

ደግሞ መላው ሰውነት ሊታመም ስለሚችል የታመመውን ክፍለ-አካል ማከሙ ይበጃል። ስለሆነም የብሔሮቹ መብት (ከመገንጠል በስተቀረ) የሚደገፍ ነው። ነገር ግን ሁሉንም የሕብረተሰብ አባላት በፖለቲካ ፓርቲዎችና በሲቪክ ማሕበራት ዙርያ መደራጀት የሚፈልጉ በብሔር ብቻ መደራጀት አለባቸው ማለት ጠቅላላ ክፍላተ-አካለትን የሚያስተናግድ ግዙፍ ሰውነትን የሚያሳምም ስለሆነ ጸረ-አብዮታዊ ድርጊት ነው። ደርጊቱ ግን ቋሚ መምርያ ከሚያወጣው መንግሥት የፈለቀ ብቻ ሳይሆን አብዮተኞች እና ተቃዋሚ ኃይል ነን ከሚሉም የመነጨ አደጋ ነው። ባሁኑ ጊዜ ለምሳሌ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቍጥራቸው አነስተኛ የሆነ አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያ-አቀፍ አጀንዳ የሚያራምዱ ሲኖሩ ፣ ብዙሃኑ ግን ከብሔር ወደ አውራጃ ከዛም አልፎ ወደ ጎጥ ስላዘቀጡ የኢትዮጵያ አብዮት አክትሟል ብንል የተሳሳተ ርቱዕነት አይደለም።

የሆኖ ሆኖ ግን አንድ አብዮት አከተመ ስንል አንጻራዊ በሆነ መንገድ ነው ፣ በጊዚያዊ መልክ አንዱ የአብዮቱ ምዕራፍ አበቃ ወይም አብዮቱ ሕዝቡ በፈለገው መንገድ ሊጓዝ አልቻለም፡ እንቅፋት አጋጠመው ማለታችን ነው እንጂ ፍጹማዊ በሆነ አባባል ሕዝባዊ አመጽ ወይም አብዮት አይፈነዳም ማለት አይደለም። እንድያውም በዚሁ ጽሑፍ መግብያ ላይ እንዳየነው ልክ እንደተኛ እሳተጎመራ ጊዜው ሲደርስ አብዮቱ መፈንዳቱ አይቀርም ፣ የሚያግደው ኃይል አይኖርም!

አሁን በቱንዝያ፡ በግብጽ እና በየመን የተቀጣጠሉት ሕዝባዊ ዓመጾች በሕዝቡ ቀስቃሽነት የተጀመሩ ለመሆናቸው አንድም ሁለትም የለውም። ለሦስቱ ዓመጾች መንስኤ የሆኑት የጋራ ምክንያቶች ደግሞ በመጥፎ የአገዛዝ ስልት ምክንያት ፍትሕ፡ ርትዕና ዴሞክራሲ በመጣሳቸውና የኑሮ ውድነትም ስለታከለበት ነው። የሦስቱ አመጾች ታሪካዊ አመጣጥና ተጨባጭ ሁኔታዎች ግን ሊለያዩ ይችላሉ።

ቱንዝያ 10 ሚልዮን ሕዝብ ብቻ ያላት አነስተኛ የሰሜን አፍሪቃ አገር ናት። ከፈርንሳይ ቅኝ ግዛት ነጻነቷን በ1956 ከተቀዳጀች በኋላ የመጀመርያው ፕረዚደንት ሓቢብ ቡርጊባ ለሃገራቸው የሚበጅ የሚያዋጣ (pragmatic) የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከመከተላቸውም በላይ ቅይጥ የኢኮኖሚ መምርያ በሃገር ውስጥ እንዲሰፍን ስላደረጉ ከሞላ ጎደል በቱንዝያ የተረጋጋ ሁኔታ ፈጥረው ነበር ማለት ይቻላል። ነገር ግን በመጀመርያ '80ዎቹ የምጣኔ ሃብታዊ ቀውስ ስለተፈጠረና የቱነዝያ ሕዝብ ደግሞ የሰላሳ ዓመት የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ስለሰለቸውና መንግሥቱም ተቀናቃኝ የመድበለ ፓርቲዎች በሕግ እንዲሰሩ ስላልፈቀደ ፣ በሕቡእ የሚንቀሳቀሱ አብዮታውያንና የእስላም አክራሪ ኃይሎች ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ ፣ የሥራ አድማም እንዲመታ አበረታቱ። ይኸውም መጠነኛ የፖለቲካ ቀውስ ፈጠረና ፕረዚደንት ቡርጊባ በ1987 ከስራ ተወግደው ጡረታ እንዲወጡ ተገደዱ። በጊዜው ጠቅላይ ሚኒስተር የነበሩ ዚን አል አቢዲን ቤን ዓሊ ፕርዚደንት ሆኑ ፣ የሕዝቡ ብሶትና ቍጣ ለማብረድ ደግሞ ቤን ዓሊ በ1988 በእስር ቤት የነበሩትን የእስላም ተንቀሳቃሽ ስብስብ ከፊቱ በኋላ የፖለቲካ ደርድር እንዲኖርም ስለፈቀዱ ሕዝቡ ከፍተኛ ተስፋ አደረገና ለአዲሱ መንግሥት ድጋፉን አሳይቷል። በተጨማሪም በ1988 አጋማሽ ላይ ቤን ዓሊ አዳዲስ ሚኒስተሮች በመሾም የድሮ ሚኒስተሮችን ተክዋቸው። በ1989 ደግሞ ብዙ ፓርቲዎች የተሳተፉበት ምርጫ ተካሄደ ፣ ግን ምርጫው በገዢው ፓርቲ ስለተጭበረበረ ቤን ዓሊ አቸናፊ ሆነው ወጡ ተባለ።

እንደገናም በተመሳሳይ መልኩ የ1994 ምርጫ ስለተጭበረበረ ቤን ዓሊ ያለምንም ተቃውሞ ተመረጡ ተባለ። ከዚህ በኋላ የለየለት አምባገነናዊ ሥርዓት በቲንዝያ አንሰራራ። ነገር ግን የቤን ዓሊ መንግሥት ወደ ውጭ የመላክ ሽቀጥ (export oriented market) የሚል አዲስ የኢኮኖሚ መምርያ በመከተል የፋብሪካ ፡ እርሻ፡ ቱሪዝም ወዘተ በሚያረካ ሁኔታ ማሳደግ ችሎ ስለነበር፡ ከሞላ ጎደል በአገሪቱ ኅብረተሰባዊ እርጋታ አምጥቶ ነበር ማለት ይቻላል።

ከላይ የተዘረዘረው የቱንዝያ የፖለቲካ አዝማምያ ዓይነተኛ የአምባገነን የአገዛዝ ስልት ለመሆኑ ማንኛውም የፖሊተካል ሳይንስ ተማሪ ይገነዘበዋል። አምባገነኖቹ የተቀነጫጨበ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ቢያደርጉም መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ግን ስለማይችሉ ሕዝቡን ማታለል አይችሉም ፣ በመሃሉ ደግሞ የምጣኔ ሃብታዊ ቀውስና የዋጋ ግሽበት ምልዓተ ሕዝቡን ሲያበሳጭ ይቆይና ድንገት ደራሹ ሕዝባዊ ዓመጽ ይፈነዳል። ዓመጹ ከገነፈለ ደግሞ የሚያቆሞው ኃይል አይኖርም። ይህ ታሪካዊ ሃቅ በቱንዝያ ስለተከሰተ ነው ደግሞ አያ ቤን ዓሊ ፈርጥጠው ወደ ሱዑድያ የሂዱት።

በቱንዝያ በእርግጥ መንግሥቱ ወድቆ በጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት ተተክቷል፣ ከስድስት ወር በኋላም ምርጫ ይኖራል ተብሏል። ነገር ግን ዓመጹ በተደራጁ አብዮተኞችና ግልጽ በሆነ ርእዮተ ዓለም የተመራ ሰላልነበረ በሃገሪቱ ውስጥ ሥር ነቀል ለውጥ ሊያመጣ አይችልም ፣ በአፍሪቃና በመካከለኛው ምስራቅ ያስከተለው እንድምታ ግን በታሪክ ከፍተኛ ምዕራፍ የሚይዝ ይሆናል። አምባገነኖች ወዮላችሁ የሚያሰኝም ነው።

የግብጽ ሕዝባዊ ዓመጽ በይዘቱ ከቱንዝያው ተመሳሳይ ሆኖ በመጠን ግን እጅግ በጣም ይለያል። ግብጽ ባገር ስፋት፡ በሕዝቡ ብዛት እንዲሁም በመንግሥት መዋቅሮች ግዙፍነትና ውስብስብነት ቱንዝያን አስሬ ያጥፈዋል። የግብጽ የጸጥታና ወታደራዊ ተቋማት በስፋታቸውና በረቂቅ ስራቸው በአፍሪቃ ተወዳዳሪ የሌላቸው ስለሆኑ በቀላሉ የሚገፈተሩ አይሆኑም አብዮታዊ ንቅናቄ 'የታሪክን ወቅት' ካልጨበጠ በስተቀረ ፣ ዓመጹ ግን ቁንጮ የመንግሥት አካላትን ማሰወገድና ማስፈረጠጥ ይችላል።

የግብጽ ዘመናዊ ኃይለኛ ወታደር ሊፈጠር የቻለው በ1952 በጀማል አብደል ናስር የተመራው የነጻ መኰንኖች መፈንቅለ መንግሥት ንጉሱን ከገለበጠ በኋላ ነው። የናስር መንግሥት ተቀዳሚ አጀንዳ ግብጽ ጠንካራ ወታደር እንዲኖራት ፣ ሕብረተሰቡን እንደገና መገንባት ፣ ልዩ ልዩ የትምህርትና የጤና ግልጋሎትን መዘርጋት ፣ ግብጽ በኢንዱስቱሪ የበለገጸችና ከጥገኝነት ነጻ የሆነች አገር እንደትሆን ማድረግ የሚያጠቃልል ነበር። ኢኮኖሚውን አስመልክቶ ግን የናስር መንግሥት መጀመርያ በምዕራቡና በምስራቁ ዓለም የታመቀ ነበር ፣ የኋላ ኋላ ግን ወደ ምስራቅ ስላዘነበለ በዓረብ ሾሻሊሰት አንድነት በተባለው ፓርቲው አማካኝነት የኢኮኖሚው ቋሚ መምርያ በማውጣት ንብረትነትን በመንግሥት እጅ እንዲወድቅ አደረገ። ስኬታማ ግን ሊሆን አልቻለም ፣ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም (IMF) ደግሞ ተጽዕኖ ደረሰበት። ግብጽ የደረሰበትን ተጽዕኖ ሳይፈታ የ1967 የእስራኤልና የዓረቦች ስድስት ቀን ጦርነት ስለተደረገ በግብጽ ኢኮኖሚ ላይ ተጨማሪ ችግር ፈጠረ ፣ የዋጋ ውድነት አገሪቷን አጥለቀለቀ።

በመጀመርያ ‘70ዎቹ ግን ግብጽ እንደገና ራሷን መገንባት ጀመረችና ምጣኔሃብቱም በመጠኑም ቢሆን ተጠናከረ ፣ በፖለቲካ ረገድም ወደ ዴሞክራስያዊ ሥርዓት በማምራት የመድበለ ፓርቲዎችም ሕጋዊነት ስለተረጋገጠ የዓረብ ሾሻሊስተ አብዮት ብቻ ሳይሆን ሌሎች ፓርቲዎች እንደ ሾሻሊስት ሊብራል ፣ ፕሮግረሲቭ ናሽናሊስት ፣ ሾሻል ዴሞክራቲክ እና ናስራዊ (የናስር ተከታዮች) ፓርቲ የተባሉት በነጻ እንዲንቀሳቀሱ ተደረገ።

እንደገና በ1978 ፕሬዚደንት ሳዳት ብሔራዊ ዴሞክራቲክ ፓርቲ የተባለውን የራሳቸው ፓርቲ ከመሰረቱ በኋላ፡ ሌላ ፓርቲ ሾሻሊስት ፓርቲ የሚባል ደግሞ እንደተቀናቀኝ የሚንቀሳቀስ ኢብራሂም ቡክሪ በተባለው ሚኒስተራቸው እንዲፈጠር አበረታቱ። ይህ ግን በተንኮል የተጠነሰሰ የፖለቲካ እቅድ ነበር ፣ ከላይ የተጠቀሱትን ተፎካካሪ ፓርቲዎችን ማዳከምና ማጥፋት ነበር። በእቅዱም መሰረት አዳከሟቸው ፣ ናስራውያንን ደግሞ ክፉኛ መቷቸው። ስለሆነም ፕሬዚደንት ሳዳት በ ሰኔ 1979 ዓ.ም. በተካሄደው ምርጫ አቸናፊ ሆነው ወጡ ተባለ። ብቻቸውን እንደ መሮጥ ነው የነበረው እና አቸነፉ ፣ እንደ ቤን ዓሊና ሌሎች የአፍሪቃ መሪዎች ቀስ በቀስ ወደ አምባገነን አገዛዝ አመሩ ግን እምበዛም አልቆዩም ፣ በገዛ ወታደሮቻቸው በ1981 ተረሸነው ተገደሉና በጊዜው ምክትል ፕሬዚደንት የነበሩ አቶ ሙባርክ በትረ ሥልጣኑን ተረክበው ከአቶ ሳዳት በእንጭጭነቱ የወረሱትን አምባገነን አገዛዝ በማጐልመስ ለሠላሳ ዓመታት ገዙ። ግብጽን ከሪፓብሊክ ወደ ንጉሳዊ አገዛዝ ለመቀየር እቅድ የነበራቸውም ይመስል ሥልጣን ለልጃቸው ለማውረስ ከጅለው ነበር። ነገር ግን የታሪክ ወቅቱ ደረሰና ሕዝባዊ ዓመጽ ከፊታቸው ተደቀነ ፣ ግብጽ ተጨናነቀች ፣ የሙባርክ መንግሥትም በመንኮታኮት እንዳለ ግልጽ ነው። ነገር ግን ልክ እንደ ቱኒዝያው ዓመጽ የግብጽ ዓመጽ አስተዋጽኦ በመጠኑም ቢሆን ሕዝብ የጠየቃቸውን የመብት፡ የዴሞክራሲና የኅብረ-ምጣኔሃብታዊ (በተለይም የስራና ምግብ) ጥያቄዎች ይመልስ ይሆናል ፣ ስር ነቀል ለውጥ ግን አያመጣም።

በማጠቃለል ፣ ለውይይት መንደርደርያ የማቀርባቸው ጥያቄዎች ቢኖሩ 1) የትኞቹ አብዮቶች ናቸው መቀበልና መደገፍ ያለብን? ደም በማፍሰስ የሚተገበሩት ስር ነቀል ለውጦች ወይስ የሰላሙን መንገድ በመከተል፡ ስር ነቀል ባይሆንም፡ በአንጻርነት ግን አመርቂ ውጤቶቹን የሚያመጡ አብየቶች? መምረጥ ከተቻለ የሰላሙ መንገድ ነው የሚመረጠው ፣ ችግሩ ግን መምረጥ አይቻልም፡ ምክንያቱም ሕዝባዊ ዓመጾች ወይም አብዮቶች ባንዳፍታና በወረቀት ንድፍ ብቻ ሊተገበሩ አይችሉም። ከላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች በይበልጥ ለማላመጥና በታሪክ ተንተርሰንም የአብዮቶች መንስኤዎችና በሕብረተሰብ ዘንድ የሚያስከትሏቸው እንድምታ አንድንገነዘብ ትንሽ ወደ ጥንታዊ የሰው ታሪክ ልመለስና ከፍ ብለን ካየናቸው ትላልቅ አብዮቶች ይልቅ ከፍልስፍናና ከኃይማኖቶች የፈለቁ የመንፈስ አውድማን የሚያንጸባርቁ (transcendental) አብዮቶች ናቸው የሰላሙን መፈክር አንግበው የተነሱት። በነገራችን ላይ ዘለቄታም ያገኙ እነዚህ አብዮቶች ናቸው።

እነዚህ ከጥንታዊ ሥልጣኔ የተቆራኙ የፍልስፍናና መንፈሳዊ አብዮቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ያንሰራሩት ከ500 ዓመተ ዓለም ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ ልደተ ክርስቶስ ባለው ጊዜ ነው። ነገር ግን ይህ ዓይነት አብዮት በግብጽም ከ3000 ዓመተ

ዓለም ጀምሮ መልህቁን ጥሎ ነበር። ለመጀመርያ ጊዜ የዓለም መንግሥትና የአምላክ መንግሥት (የአማልክት መንግሥታት) ግኑኝነት እንዳላቸው ለማሳየት የመከሩት ጥንታውያን ግበጾች ናቸው። እንድያውም የፈጣሪ ጽንሰሓሳብ የተጀመረው በግብጻውያን ነው ፣ የአይሁዶች ኃይማኖት ከግብጹ ኃይማኖት የፈለቀ ነው ፣ ክርስትና ደግሞ አዲስ መንፈሳዊ ራእይ (አዲስ ኪዳን) እና የአይሁዶቹም ኃይማኖት (ብሉይ ኪዳን) በማጠቃለል የተደራጀ ኃይማኖት ሆነ። እነዚህ ሦስት ትላልቅ ኃይማኖቶች ታድያ የሰማዩ ጌታ ወይም የእግዚአብሔር ታላቅነት ራእይ (ontological vision) በመስበክና በማስተማር ብሎም ተቋማት በመመስረት ሰፊውን ሕዝብ በሰላም የአብዮቱ ተከታይ እንዲሆን አደረጉ።

በተመሳሳይ መልኩ ይህ ፍልስፍና-ኃይማኖት ነክ አብዮት በጥንታዊት ግሪክ ፣ በመጠኑም ቢሆን በጥንታዊት ፐርዥያ ወይም ኢራን (የዛሮስትራ ተከታዮች) ፣ በሃፀያዊት ቻይና (የቡዳ ተከታዮች) ፣ በህንድ (የቡዳና የሂንዱ ተከታዮች) ፣ እንዲሁም ቆየት ብሎ በሱዕዲ ዓረብያ የጀመረው የእስላም ኃይማኖት አድማሳዊ ጸባይ እንዳለውና መስፋት እንደቻለ የምናውቀው ጉዳይ ነው።

እነዚህ ታላላቅ ኃይማኖቶች (አልፎ አልፎ ኃይልና ጡጫ ቢጠቀሙም) ከሞላ ጎደል ግባቸውን በሰላም ነው ያገባደዱት። ለዚህም ነው በብልዮን የሚቆጠሩ ምእመናን ማፍራት የቻሉት። እነዚህ ታላላቅ ኃይማኖቶች የመንፈስ ሰበካ ብቻ አይደለም ያጠናቀቁት ፣ ትምህርት ቤቶች ከፍተዋል ፣ የጤና ጣብያዎች መስርተዋል ፣የልማት አውታሮችን ዘርግተዋል። ከሁሉም በላይ ግን የሕብረተሰብ አባላትን በግብረገብነት እንዲታነጹና ለፍትሕ እንዲቆሙ ስለሰበኳቸው ሰው ሁሉ ከመጥፎ ድርጊት (ከሓሰትና ስርቆት እስከ ቅተለተ ነብስ) እዲታገድ አድርገውታል። ባስተሳሰብም በተግባርም ከትላልቆቹ ኃይማኖት ውጭ የሚኖር ሰው ወይም ስብስብ ግን ሰውን ለመበደል ወደ ኋላ አይልም ፣ ደም ከማፍሰስም አይቆጠብም። ለዚህም ነው ከፍ ብለን የተወያየንባቸው አብዮቶች (ከእንግሊዙ እስከ ቻይናው እና እስከ የኛው የ'66ቱ) በሺዎች ወይም በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች የገደሉት ወይም ያስገደሉት። ስለሆነም የሰላሙ መንገድ ነው የሚመረጠው ፣ መምረጥ ከተቻለ። የሕዝብ ዓመጽ ወይም አብዮት እንደገና ኢትዮጵያ ውስጥ መደንፋቱ አይቀርም ፣ እኛ ስለፈለግነው ሳይሆን የታሪክን ሕግ ተከትሎ የሚፈነዳ የሰው ተግባር ስለሆነ ነው። ለማይቀር የታሪክ ወቅት ታድያ በቅድምያ ስነ-ልቦናዊና ድርጅታዊ ዝግጅቶቹን ማድረክ ያስፈልጋል የሕዝቡን ዓመጽ ፈር ለማስያዝና ስኬታማ እንዲሆን ከተፈለገ። ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ እንዳይሆን ደግሞ ኮስታራና ትጉህ ዝግጁነትን ይጠይቃል።

All Rights Reserved. Copyright © IDEA Inc. 2011. Dr. Ghelawdewos Araia can be contacted for educational and constructive feedback via dr.garaia@africanidea.org